# እውን የትግራይ ህዝብ በሌሎች ህዝቦች ተጠልቷልን?

## ክፍል ሁለት

ሀይላይ ማሙዶ 25/04/2010 ዓ/ም

ውድ አንባቢዎች በክፍል አንድ ፅሁፍ የአቶ ፀጋ አስማረ ስለ ዘር ፖለቲካ መኖር አስመልክተው ያነሱትን ሀሳብ በመጠኑም ቢሆን ምላሽ ለመስጠት ተሞክሯል። አሁን በዚህ ክፍል ሁለት በመፍትሄነት ያስቀመጡትን ሀሳብ የሚመልስ ፅሁፍ እንደሚቀጥለው ይቀርባል። መልካም ንባብ፤-

**2. ህዝብ ከህዝብ ጋር መቼም ቢሆን አይጣላም**

በሪፖርተር ጋዜጣ የተነሳው የወቅታዊ ችግሩን የመፍተሄ ሀሳብ አስመልክቶ የቀረበላቸው ጥያቄ ለመመለስ አቶ ፀጋ የሰጡት አስተያየት በጣም አስገራሚና ቁልጭ ብሎ በአንድ ህዝብ (በትግራይ ህዝብ) ላይ ጥላቻ እንዳላቸው የሚያሳይ መሆኑ ነው። በርግጥ ስለ አንድ ጉዳያ ያለህን መነሻ ምክንያት የተዛባ ከሆነ የምታስቀምጠው መፍትሄም የተዛባ እንደሚሆን ይታመናል።

በአለም ሆነ በሀገራችን ታሪክ አንድ ህዝብ በሌላው ህዝብ ላይ ጥላቻ አሳድሮ እንደማያውቅ የታወቀ ነው። በርግጥ እንደ ሂትለርና ሞሶሎኒ የመሳሰሉትን ግለሰቦች አንድን ህዝብ ሰበብ በማድረግ ሌላውን ህዝብ የማጥፋት ወይም የማጥቃት ተግባር ሲያከናውኑ እንደነበሩ ይታወቃል። ይህ ግን ህዝብ ከህዝብ መጣላትን አያሳይም።

በሀገራችን ታሪክም ገዢዎች ለረጅም ጊዜ የህዝቦች ማንነት በመጨፍለቅ ሲገዙና አልፎም ዘርን የማጥፋት አላማ ይዘው ሲንቀሳቀሱ እንደነበር የታወቀ ነው። የቅርብ ጊዜ እንኳን እንደ እነ አቶ ፀጋ ያሉትን ሰዎች የሚያልሙት የአንድ ሀገር፣ አንድ ቋንቋ፣ ወዘተ በማቀንቀን አንድ አገዛዝ የነበረው የደርግ ስርአት ምን ያህል በህዝቦች ማምነት ለማጥፋትና ህዝብ እንደ ህዝብ ለመጨፍጨፍ ይጠቀምበት እንደነበር በእኛና በአቶ ፀጋ እድሜ አይተነዋል።

ይህ ተግባር ግን መሪዎች የአንድ ህዝብ ስያሜ ይዘው የፈፀሙት አረመኔነት እንጂ ህዝብ ከህዝብ ጋር ጥላቻ ኖሮት የተፈፀመ አይደለም አልነበረምም። ገዢዎች ስልጣናቸውን ለማቆየት ሲሉ በህዝቦች መሀከል መቃቃር ለመፍጠር ጥረት ቢያደርጉም፤ የእከሌ ህዝብ ዘምቶ እንጂ ተዘምቶ አያውቅም፤ ቢሉም ሰሚ ጆሮ ሳይሰጣቸው ህዝቦች በጋራ ሆነው ነበር ጨቋኛቸውን ለማስወገድ የታገሉት። ስለሆነም በወቅቱ የነበረው ጭቆና ከማንኛውም ህዝብ ጋር ማያያዝ አልተቻለም አይገባምም።

ጤነኛና የማገናዘብ ህሊና ያለው ሰው አሁን ያለው የኢህአዴግ መንግስት ችግሮችም ከራሱ የድርጅቱ ማለትም (ከህወሀት፣ ብአዴን፣ ኦህዴድና ደኢህዴን) ጋር የሚያያዝ እንጂ ነጥሎ ለአንድ ብሔር የሚሰጥ ችግር አድርጎ መመልከት ፈፅሞ ተገቢ ሊሆን አይችልም። ስለሆነም መፍትሄ መምጣት ያለበትም አንድን ብሔር ተጠያቂ ሌላው ጠያቂ ሆኖ በመወቃቀስ ሳይሆን በጋራ ሁሉም ብሄሮች የመፍትሄው አካል ሆነው የጋራ እሴቶቻቸውን የማጎልበትና የእርስ በእርስ ግንኙነቱ የማጠናከር ተግባር በቀጣይነት መፈፀም ሲቻል ነው።

ከላይ እንደገለፅኩት በታሪካችን ውስጥ ህዝብ ከህዝብ ጋር ተጣልቶ እንደማያውቅ የታወቅ ሲሆን በአሁን ጊዜም በህዝቦች መሀከል መጠራጠር ሊፈጥሩ የሚችሉ የተለያዩ የታቀዱ የስም ማጥፋት ስራዎች ለ26 አመታት ያክል ሙሁራን በተባሉ ሰዎች እየተሰራበት የነበረ ውጤት ቢሆንም በመሰረቱ ግን ህዝብ ለህዝብ የተፈጠረ መጠላላት እንደሌለ አሳምረን ማወቅ ይገባናል። አቶ ፀጋዎች እንደ መፍትሄ ብለው የገለፁት የትግራይ ህዝብ በኦሮሞና አማራ ህዝብ የተጠላ አስመስሎ

ማቅረብም ሆን ተብሎ ለረጅም ጊዜ የተሰራበት የስም ማጥፋት እና በትግራይ ህዝብ ያለውን የግል ጥላቻ አካል ካልሆነ በስተቀር መሬት ላይ ያለ አይደልም።

አቶ ፀጋ የትግራይ ህዝብ በአማራና በኦሮሞ ህዝብ እንደተጠላ ለመናገር ያስቻላቸው ድፍረም እንዴት እንደመጣላቸው ለማወቅ አስቸጋሪ ነው። እውን የኦሮሞ ወይም የአማራ ህዝብ ሌላ ህዝብ የመጥላት ስነልቦና ወይም ባህል አለው ወይ? ብለን ብንጠይቅ ለእንደኔው በሁለቱም ህዝቦች መሀከል ሆኖ የደርግ ስርአትና ኦነግ ለማጥፋት የተደረገው እንቅስቃሴ ተሳትፎ የነበረውን የህዝቦቹ ፍቅር ያየ ሰው ለማሳመን የሚችል አይደለም። ለዚህም ነው ይህ የአቶ ፀጋዎች አስተሳሰብ የግላቸው እንጂ የኦሮሞ ወይም የአማራ ህዝብ የሚወክ አይደለም የምለው።

እስቲ የቆየውን ፍቅር እንተወው እና አሁን ተፈጥሯል የተባለውን የብሔር ግጭት ነጥሎ የትግራይ ብሔር ከመጥላት ጋር እንዴት ይያያዛል? ሌሎች ብሔሮች ላይም እኮ ኢላማ ተደርገዋል፤ አሁን በኦሮምያ ውስጥ የሚኖሩት በርካታ የትግራይ ተወላጆች አሉ፤ እነሱ ማን ነው አቅፎ እያኖራቸው ያለው? የኦሮሞ ህዝብ አይደለም እንዴ? ግለሰቦች ሆን ብለው ወይም በእንደእነ አቶ ፀጋ ሀሳብ ተታለው ጥቃት ሲያደርሱ እኮ ህዝቡ ነው እየጠበቃቸው ያለው። አረ ተው አቶ ፀጋ ጎንደር ላይ የትግራይ ተወላጆች በግፍ ሲፈናቀሉና ሲገደሉ እዛ የቀሩት የትግራይ ተወላጆች ማን ነበር ያዳናቸው? ካላወቁና ማወቅ ከፈለጉ ልንገርዎት፤ የክልሉ መስተዳድር ወይም ዞኑ እንዳይመስልዎት የጎንደር ህዝብ ነው። መስተዳድሩና ዞኑማ ምን እንዳደረጉ ጊዜ ሁሉም ነገር ግልፅ ያደርገዋል። እዚህ አልገልፀውም።

መቸም የፀጥታ አካላት በኦሮሚያና አማራ ክልል ያሉ የትግራይ ተወላጆች እየጠበቁዋቸው ስለሆነ እንዳይሉና እንዳልስቅብዎት። ህዝብ ጥላቻ ካለው ማንም እንደማያቆመው በእድሜ ዘመኔ አይቻለሁና ረጋ ብለው ያስቡ። በትግራይ ህዝብ ያለዎትን ጥላቻ የአማራና የኦሮሞ ህዝብ ጥላቻ አድርገው አይመለከቱት።

በመሆኑም የትግራይ ህዝብ እንደማንኛውም ህዝብ ሌላውን ህዝብ የሚጠላ ስላልሆነ እንዲሁም በሌላው ህዝብ እጠላለሁ ብሎ አያምንም። ስለሆነም የአማራ ወይም የኦሮሞ ህዝብ ለምን ጠላኝ ብሎ የሚያስብበት የደቂቃ ጊዜም የለውም። አሁን ለተፈጠረው ሀገራዊ ችግርም ከሌሎች የሀገራችን ህዝቦች ጋር በመተባበር መፍትሄ በመስጠት የጀመረውን የለውጥ ጉዞ የማስቀጠል ድርሻው እንደሚወጣ ያምናል እንጂ።

እዚህ ላይ ደግሞ ሁለተኛ ትዝብት በጋዜጠኛው ላይ ላስቀምጥ የትግራይ ህዝብ ለምን በኦሮሞና በአማራ ህዝብ ተጠላሁ ብሎ ይጠይቅ ሲሉት እንዴት አንድ ህዝብ ሌላውን ህዝብ ይጠላል ብሎ አይጠይቃቸውም እንዴ? ወይስ ይህንን አመለካከትም ጋዜጣው ይጋራዋል? ብለን ብንጠይቅ ይገርመው ይሆን?

ወደ ቀደመው እንመለስ አቶ ፀጋ ይህ የህዝብን በህዝብ የመጠላት አባዜ ምናልባት ከዚህ በፊትም በታቀደ መንገድ ሲሰራበት የነበረ ህዝቦች እርስ በርሳቸው እንዲጠራጠሩና ወደ ግጭት እንዲገቡ የማድረግ ተግባር አካል የሆነ አስተሳሰብ ያንፀባረቁ ይመስለኛል። በዚህ አስተያየታቸው ተነስቶ ሰው እንዲጠራጠርና የሀገራችን ብሔር ብሔረሰቦች በጋራ ሆነው ለመፍትሄ እንዳይንቀሳቀሱ ለማድረግ ታስቦ አንዱ የሚጠላ ሌላው የተጠላ አድርጎ የመግለፅ ስራ የሚሰራ ያለው። በተለይም ከደርግ ውድቀት ጀምሮ እየተሰበከ ያለው “የትግራይ የበላይነት” እየተባለ የሚነዛው ወሬ መንግስት የተመቸው ይመስል ተገቢውን ምላሽ ሳይሰጥበት የቆየው እነአቶ ፀጋም የተጋባባቸው በመሆኑ የተፈጠረ ጥላቻ ይመስላል።

ሌላው አቶ ፀጋ በዚህ የመፍትሄ ሀሳባቸው የትግራይ ህዝብ ለውጥ ከሚፈልጉ ህዝቦች ጎን መቆም አለበት ይላሉ። ምን አይነት ለውጥ ይሆን የፈለጉት? ያለውን ስርአት አፍርሶ ወደ ኋላ መመለስ ይሆን? ወይስ ባለው የመደመር? የአቶ ፀጋ የትግራይ ህዝብ ጥላቻ ብቻ ሳይሆን ንቀታቸውም ያሳዩበት ሀሳብ ነው። አቶ ፀጋ የትግራይ ህዝብ ለውጥ ፈላጊ አይደለም፤ ባለበት የቆመ ነው፤ ሌሎች ህዝቦች ግን ለውጥ ፈላጊ ናቸው፤ በሚል ይገልፁታል። ይገርማል አንዱ የመከፋፋል አላማቸው ይሆናል።

በመሰረቱ አንድ ሰው ወይም ማህበረሰብ በአመፅ ወይም ህጋዊ ባልሆነ መንገድ ግርግር ካልፈጠረ ለውጥ ፈላጊ አይደለም የሚል እምነት ከተያዘ የተሳሳተ ነው የሚሆነው። አሁን በሀገራችን እየተፈጠሩ ያሉ በተለያዩ አከባቢዎች የህዝቦች የለውጥ ፍላጎትና የቡድኖች ግርግር መፍጠር ለያይተን ካልተመለከትነው የተሳሳተ ድምዳሜ ነው የሚያደርሰን።

በርግጥ የሀገራችን ህዝቦች ያለው መፋዘዝ ተወግዶ አዲስ ለውጥ እንዲመጣ ያሉትን ችግሮች ተወግደው የተሻለ መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ በመፈለግ የተለያዩ የመብት ጥያቄዎች በሰላማዊ መንገድ እያነሱ ናቸው። በሌላ በኩል ደግሞ ይህንን የህዝቦች ጥያቄ ለራሳቸው አላማ ያዞሩትና በሀገራችን ሰላም እንዳይኖር እንዲሁም ቀኝኋላ እንድንዞር የሚፈልጉ ሀይሎች ደግሞ ግርግሩን እያቀነባበሩት ይገኛሉ። መቼስ የሚፈሰው ዶላር አፍ ቢኖረው ስንት ጉድ በነገረን?

የትግራይ ህዝብ በሁለት ዱላ እየተመታ ግን ሁሉም ነገር በትእግስት እያስተናገደ ያለ ህዝብ ነው። ይህ ህዝብ ለማንነቱና ለክብሩ ከሌሎች የሀገራችን ህዝቦች ጋር በእኩልነትና በጋራ ሀገሩን ለማሳደግ የሚያስችለው ስርአት ለመፍጠር ውድ ልጆቹ በህይወትና በአካል መቁሰል የገበረ እንደመሆኑ በአንድ በኩል ይህንን ጨቋኝ ስርአት ማፍረሱን ያልወደዱለት እንደነ አቶ ፀጋ ያሉ ሰዎች፣ በሌላ በኩል ራሱ ያሳደጋቸው እና ስልጣን ሲይዙ ከድተውት ፍትህ ማስፈን ያቃታቸው ልጆቹ በኩል እየተጎዳ ይገኛል። በተለይም ከደርግ ውድቀት ጀምሮ ሻእብያ ሲያገዘው የነበረ የመሀል ሀገር ሀብት ወደ ትግራይ የሄደ በማስመሰል አሉባልታ ሲወራ ተገቢውን ምላሽ ሳይሰጥበት መዝለቁ ሳይበላ እንደበላ እየተቆጠረ እየተጎዳ ያለ ህዝብ ነው።

እውቁ የትግርኛ ዘፋኝ ወዲ ሮሚተ በቅርብ ባወጣው ዘፈኑ እንዳለው "... አንተ የትግራይ ህዝብ እንዴት ነህ ያለሀው ብልህ አውቀዋለሁ ምላሽህ ደህናነኝ እንደምትለኝ፣ እኔ ግን...." (የአማርኛ ትርጉም የኔ ኔው ካበላሸሁትም ወዲ ሮሚተን ይቅርታ እላለሁ) እዚህ ላይ ግልፅ መሆን ያለብኝ የትግራይ ህዝብ ከሌላው የተለየ ነው ሌላው ህዝብ እንዲህ አይልም እያልኩ እንዳልሆነ ነው። በእነ አቶ ፀጋ ዋና ኢላማ ተደርጎ ያለው የትግራይ ህዝብ በመሆኑ የተገለፀ መሆኑ ይታወቅልኝ።

እንቀጥል ታድያ የትግራይ ህዝብ ለውጥ ፈላጊ መሆኑም ለማሳየት በተለያየ ጊዜ በክልሉ ያለው ድርጅት ውስጡን እንዲፈትሽ፣ በየቦታው ያሉትን ሹመኞችም ህግን እንዲያከብሩ፣ ፍትህ እንዲሰፍን ለማድረግ በተለያዩ መድረኮች ሰላማዊ በሆነ መንገድ እንደ ሌሎች ክልሎች ሲጠይቅ የነበረ እና አሁንም ህወሀት ላይ ግፊት እያደረገ ያለ ህዝብ ነው። ከዚህ አልፎም በሀገራችን ላይ ለውጥ እንዲመጣ የበኩሉን ድርሻ ለመወጣት ጥረት እያደረገ ያለ ለዚህም በተለያዩ ክልሎች በልጆቹ ኢላማ ያደረገ ጥቃት በሚደርስበት ጊዜ " ለምጣዱ ሲባል አይጥዋን ትለፍ" እንደሚባለው በትእግስት እያለፈ ያለ ህዝብ ነው። ይህም በየክልሉ ያሉ ህዝቦች ይህንን ጥቃት ይከላከላሉ የሚል እምነት ስላለውም ጭምር ይመስለኛል።

ለዚህ ግን እንደ አቶ ፀጋ አይነት ሰዎች የትግራይ ህዝብ ለውጥ የማይፈልግ ራሱን ከሌሎች ህዝቦች የተነጠለ አድርጎ ምስል እየተሰጠው የሚገኘው። እዚህ ላይ አንድ ጉዳይ ሳንሳ ዝርዝር ምላሽ በሌላ ጊዜ የምመለስበት ሆኖ አቶ ልደቱ የተባሉ እውቁ ፖለቲከኛ በአንድ ENN የተባለ የቴለቪዥን ጣብያ የህዝብ ድምፅ በሚል ፕሮግራም ቀርበው ለትግራይ ህዝብ ያቀረቡት ጥያቄ ከሳቸው የማልጠብቀው ሆኖ አግኝቸው ገርሞኝ ያለፍኩት ነበር። አቶ ልደቱ በትግራይ ውስጥ ለምን አንድ ተቃዋሚ መመረጥ እንዳልተቻለ የትግራይ ህዝብ ራሱን እንዲጠይቅ ኳስዋን ለህዝቡ አቀበሉት። ይህንን ያነሳሁት የነአቶ ፀጋ ሀሳብ የተጋራ በመሆኑ ነው።

መቸስ ህዝቡ በአንድ ላይ ተሰብስቦ ምላሽ እንዲሰጣቸው አቶ ልደቱም አይጠብቁምና እስቲ ራሳቸው ምላሻቸው ይስጡን፣ እስቲ እንደ አቶ ፀጋ ያሉ ሰዎች ህዝብን በአንድ ላይ ጠቅልሎ የሚጠላ ያለበት፣ እንደ እቃ ሳሙና እያለ የሚሳደብ "ሙሁር" ያለበት፣ የትግራይ ህዝብና ህወሀት የተባለ የፖለቲካ ድርጅት ለይቶ ማየት የተሳነው ተቃዋሚ እያለ፣ ህዝቡ እንዴት ሊመርጠው ይችላል? እንዴት የምጠላህን፣ የሚሰድብህን፣ ለምን አትመርጥም ይባላል? እንዴ ሌላው ይቅርና በጉያው ውስጥ የነበሩ እነ አረና ሄደው ሄደው ህዝቡን አይደል ጠላት ያደረጉት? ይህ እኮ ነው ህዝብን በአንድ ላይ በጥላቻ አትፈርጁት እያልን ያለነው ጎበዝ።

**ሲጠቃለል**

ይህን ፅሁፍ ስጀምር ምናልባት ሁለት ገፅ ብፅፍ ብዬ ነበር የተነሳሁት። እንዲህ የሚረዝም አልመሰለኝም። ታድያ በውስጤ ለካ ብዙ አለ አሁንም ፃፍ ፃፍ ይለኛል። ግን እስኪ ይቆየን ፈጣሪ ጊዜ ከሰጠንና አይጋዎች አሁን የያዙት አካሄድ ከቀጠሉበት መፃፋችን አይቀርም እንግዲህ የዛ ሰው ይበለን።

ምናልባት የአቶ ፀጋ አስማረ በሪፖርተር ጋዜጣ ይህንን የተዘባ አመለካከት መነሻ ሆኖኝ፤ በዚህ ዙርያ ከዚህ በፊትም የትግራይ ህዝብ ኢላማ አድርገው ጀኖሳይድ እንዲፈፀም እንዳነሳሱ “ጋዜጠኞች”ለምን የትግራይ ህዝብ ለይቶ እንደ ጠላት የሚያዩ ግለሰቦች አጠቃላይ የህዝብ አመለካከት አድርገው ያዩታል የሚለውን ውስጤን ላይ የፈጠሩት ጥያቄ ለመግለፅ አስችሎኛል ብዬ አስባለሁ።

ውድ አይጋዎች ይህንን ፅሁፍ ስፅፍ ምናልባት የመጀመሪያ ስለሆነ ብዙ ችግሮች እንደሚኖሩት አምናለሁ። በሂደት በሚሰጡኝ አስተያየቶች ይበልጥ እየተሻሻለ ይሄዳል የሚል እምነት ጭምር አለኝ። በተለይ የናንተ ፎረም የተለያዩ የሀሳብ ልዩነቶችን ሳታዳሉ በነፃነት ፅሁፎች ስታስተናግዱ ሳይ ይህች ፅሁፍ እጅ ማፍታቻ ትሆነ ዘንድ ስልካት እንደምታስተናግዱኝ በመተማመን ነው። ምናልባት ማን ያውቃል በዚህ መነሻነት ወደ ተሻለ የሀሳብ ሙግት ልገባ እችልም ይሆናል። በመጨረሻ ይህንን ፅሁፍ ታትሞ የምታነቡ ታዳሚዎች ጊዜያችሁን ሰጥታችሁ ስላነበባችሁት እያመሰገንኩ ለምትሰጡት አስተያየት ለማስተናገድ ዝግጁ መሆኔን እገልፃለሁ።

**ሰላም ለሁላችን ይሁን፤**